# ሀገራዊ ጥቅማችንን ማስከበር የዜግነት ግዴታችን ነው!

**ሱራፌል በለጠ 01/25/14**

ሀገራዊ የፀረ - ድህነት ትግሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ ሄዶ ለዘመናት ከምንታወቅበት የረሃብና የድህነት መገለጫነት ወደ ፈጣን ዕድገት ተምሳሌትነት በመሸጋገር ላይ እንደምንገኝ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡ የዚህ ትግላችን አካል የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብም በመላው የሀገራችን ዜጎች ንቁ ተሳትፎና ጥረት ታጅቦ ዛሬ በሚገኝበት ደረጃ ላይ መድረስ ችሏል፡፡ በርግጥ አባይ የመላው የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቁጭት ስለመሆኑ ለዘመናት ተገድቦ የቆየው በአባይ ውኃ የመጠቀም መብታችንን ለማስከበር የተካሄደው ትግል “በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ” ለፍሬ የመብቃቱ ጉዳይ ሲበሰር ያሳየነው ስሜትና የሰጠነው ምላሽ በማስረጃነት መጥቀሱ ከበቂ በላይ ነው፡፡

በአባይ ውኃ የመጠቀም መብታችንን ሳናስከብር ዘመናትን ልንዘልቅ የተገደድንበት ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ቅሉ፤ ዕርዳታና ድጋፍ እንዳናገኝ የተካሄደብንን ደባ ግን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ላይ ሆነን ልንዘነጋው የምንችል አይመስለኝም፡፡ በርግጥ ችግሩን ማወቅ አንድ ጉዳይ ነው፤ ለችግሩ እልባት ለመስጠት መላው ዜጋ ያሳየው ቁርጠኝነትም እንዲሁ፡፡ ይሁን እንጂ በውኃው  የመጠቀም መብታችንን ለማስከበር የምናካሂደው ትግል ሊሳካ የሚችለው ጥረታችንን ለማደናቀፍ የሚሸረቡ ሴራዎችን ለማክሸፍ በምናካሂደው ሁለንተናዊ የነቃ ተሳትፎ መሆኑ መዘንጋት የሚገባው አይመስለኝም፡፡

“ነገርን ነገር ያነሳዋል” እንዲሉ አበው፤ የግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሀገራቸው ወቅታዊ ሁኔታና በአባይ ወንዝ ጉዳይ ለመወያየት አስመራ ገቡ የሚል መረጃ በቅርቡ በፌስ ቡክ ለንባብ መብቃቱን አስታውሳለሁ፡፡ ታዲያ መረጃውን ተከትሎ በኢትዮጵያውያን የሰፈሩ አስተያየቶች ህዝባችን ለግድቡ ግንባታ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያመላክቱ መሆናቸው የሚያኮራ ቢሆንም፤ የአስተያየት ሰጪዎቹ ቁጥር አናሳነት ግን በዘርፉ ያለን ተሳትፎ እጅጉን አሳሳቢ እንደሆነ የሚያመላክት ይመስለኛል፡፡

ከዚህ አኳያ በውኃው የመጠቀም ፍላጎታችን እንዲሁም ጥረታችን ምንም እንኳን ከፍተኛ መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም በተለይ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳወቅና በማሳመን ረገድ የመገናኛ ብዙሃንና የዜግነት ኃላፊነታችንን ለመወጣት የምናካሂደው ጥረት እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ ሁሉም ዜጋ በዚህ ዘርፍ ትልቅ ሥራ የሚጠብቀው ይመስለኛል።

በርግጥ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ የሚቀርቡ ዘገባዎችም ይሁን የምሁራኖቻችን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አናሳ መሆን በተደጋጋሚ እየተገለጸ የሚገኝ እውነታ ነው፡፡ ከዚህ በተገላቢጦሽ ደግሞ በግብጾች አማካኝነት ግንባታውን ለማስቆም የሚካሄደው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ የቀቢፀ-ተስፋ ሙከራ እየተጠናከረ የመምጣቱ ጉዳይ የአደባባይ ምስጢር በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

ታዲያ ለዜጎች የጋራ ፍላጎት ምላሽ ለሚሰጠው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስኬታማነት ከምናደርገው የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ በተጨማሪ ዲፕሎማሲያዊ ጥረታችንን አጠናክረን የመቀጠል ዜግነታዊ ኃላፊነትና ግዴታችንን በቁርጠኝነት መወጣት የተሳነን ለምን ይሆን?...ሀገራዊ ሚዲያዎቻችን በተለይም የግሉ ሚዲያ ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ የልማት አጀንዳ ትኩረት የመስጠት አቅሙ ለምን ከዳቸው?... ምላሹ በእነርሱ እጅ ቢሆንም የጉዳዩ እውነታነት ግን ቅንጣት ያህል አያጠራጥርም፡፡

መቼም የሆድ ነገር ሆድ መቁረጡ አይቀሬ ነውና ስለ አባይ ስንዘምር፣ ስናዜም ዘመናት መቆጠራቸው የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ በርግጥም አባይ ምንም እንኳን ሳንጠቀምበት ዛሬ ላይ ብንደርስም፤ በስንኝ ቋጠሮ አንዴ ስናሞግሰው ሌላ ጊዜ ደግሞ ስንወርፈው፣ በዜማ ተቀኝተን "የአባይን ደግነት" ከትውልድ ወደ ትውልድ ስናሸጋግር፣ "የአባይን ልጅ ውኃ ጠማው" በሚል አባባልም ስንኮራበት መክረማችንን እኛው ምስክሮች ነን፡፡

ይሁንና ይህ ሁሉ እኛው ለእኛው እንጂ ልክ እንደ ግብጾች ከአጽናፍ አጽናፍ ለማድረስ አልዳዳንም፣ በህጻናት ልጆቻችን አእምሮም እንዲቀረጽ ለቅጽበት እንኳን ሞክረን አናውቅም፣ ለምን ይሆን?...መቼም ሀገራዊ ፋይዳው የትየለሌ መሆኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡ ታዲያ አባይ ውኃ፣ አባይ ምግብ፣ አባይ የኃይል ምንጭ እንዲሁም አባይ የዕድገት መሰረት መሆኑን ለዓለም ማሳወቁን ያልገፋንበት ምክንያት ምንድነው? መቼም ዕውቀት አጠር ነን የሚል ምላሽ የሚሰጥ አንድም ዜጋ ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡

ታዲያ እንደ እኔ… እንደኔ  አብዛኛው የተማረ የሰው ሃይል የፌስ ቡክ ተጠቃሚ በሆነበት በአሁኑ ጊዜ ይህ መሰሉን የህልውና ጉዳይ ከማንሳትና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአባይን ሀገራዊ ፋይዳና የመጠቀም መብታችንን ከአድማስ አድማስ ከማድረስ ይልቅ፤ ጠቀሜታቸው ያን ያህል ባልሆኑ አጀንዳዎች ላይ መብከንከኑ ዕውቀትና ጊዜን ከማባከን የዘለለ ፋይዳ የለውም ባይ ነኝ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግብጾች አባይን የእስትንፋስ ያህል ቆጥረው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አባይን በብቸኝነት የመጠቀም ጉዳይ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ፀጋ መሆኑን ሊያሳምኑ ሲሞክሩ መስተዋላቸው "እኛስ ለምን …?" የሚል ጥያቄ ያጭራል፡፡

መቼም እያንዳንዱ የግብጽ ዜጋ ስለ አባይ ቢጠየቅ ከሞላ ጎደል የሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ደግሞ የወላጆች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን ውለታ ብዙ መሆኑ ነው የሚነገረው፡፡ እንደሚታወቀው ለማንኛውም ሰው አመለካከትና ባህሪ መሰረቱ ቤተሰብ፣ ማህብረሰብ ብሎም ሀገር ነው፡፡ ለማንም ሰው አስተሳሰብና ባህሪ መልካምነትም ሆነ መጥፎነት የእነዚህ አካላት ድርሻ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝ የማህበረሰብ ሳይንስ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ እናም አንድ ግብፃዊ ዜጋ ከህጻንነቱ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ የሚነገረው የአባይና የግብጽን ቁርኝት፣ ከአባይ ውጭ የመኖር ተስፋ እንደሌለው ብሎም "የአባይን መንካት" የማይታሰብ ተግባርና ሃቅ ነው ብሎ ቢያስብ የሚገርም አይሆንም፡፡ ምንም እንኳን ይህ "እኛ እንብላ፣ እናንተ ግን ተራቡ" የሚል የቅኝ ገዥዎች ኋላ ቀርና ኢ-ፍትሐዊ አስተሳሰብ በምድርም ይሁን በሰማይ ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም።

ወደ እኛው ስንመጣ ደግሞ ምንም እንኳን ቤተሰባችን፣ ማህብረሰባችንና መገናኛ ብዙሃናችን "አባይ የዕድገታችን መሰረት" እንደሆነና በውኃው የመጠቀም መብት እንዳለን እያሰረዱን ለዚህ ተግባራዊነት የመንቀሳቀስ አመለካከትና አስተሳሰብ በመፍጠር ላይ ቢሆኑም፤ ይህን ያህል አርኪ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። ታዲያ እዚህ ላይ ከማህበረሰቡ ትውፊቶች የገነባነው አስተሳሰብ የለም ብሎ መደምደም ይቻላል እያልኩ አይደለም፡፡ ለምን ቢባል በአባይ ጉዳይ ዙሪያ ስሜቱ የማይነካ ዜጋ ስለሌለ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር፣ እኛ ጋ የደረሱ አባይ ነክ ዜማዎች፣ የስንኝ ቋጠሮዎች፣ ፉከራዎችና ሽለላዎች…ወዘተ. በርካታ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር የአባይ ወንዝ ረጅም ከመሆኑ የተነሳ የሚያካልለውና የሚሸፍነው የሀገራችን ክፍልም ብዙ በመሆኑ አብዛኞቻችን ከልጅነት እስከ እውቀት ከአባይ ጋር ያለን ግንኙነት ቀላል የሚባል

አይደለም፡፡ ታዲያ ከእነዚህ ዕውነታዎች ስንነሳ ስለ አባይ ይበልጥ አለማስተዋወቃችን ቁጭት ላይ የሚጥል ይመስለኛል።

እናም ከዚህ ሃቅ በመነሳት የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ስለ አባይ ለመናገር ጊዜው አልረፈደም ባይ ነኝ። እናም ብሔራዊ ጥቅማችን ከማስከበር አኳያ እንደ ዜጋ ድምፃችንን ከፍ አድርገን ለዓለም ማስረዳት ይኖርብናል–አባይ ለእኛም የህይወታችንና የመለወጣችን ብሎም የሀገራዊ ህዳሴያችን መሰረት ነውና። አዎ! የአባይ ሀገራዊ ፋይዳ ዘርፈ ብዙ መሆኑንና ለእያንዳንዳችን የኑሮ ደረጃ መሻሻል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በተለይም የፀረ - ድህነት ትግላችን ጥረት የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፋይዳዎችን ስንመለከት በመጀመሪያ በሀገራችን ለተጀመረው የፀረ - ድህነት ትግል ስኬታማነት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ሁላችንም እንገነዘበዋለን፡፡ ምክንያቱም ለታላቁ ህዳሴ ግድብ የሚመነጨው የኤሌትሪክ ኃይል በመጀመሪያ በሀገሪቱ እየተስፋፋ ለሚገኘው ኢንቨስትመንት በቂ ምላሽ መስጠት የሚችል ስለሆነ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የማንኛውም ኢንቨስተር ቀዳሚው ጥያቄ የኃይል አቅርቦት ነው፡፡ በቂ የኃይል አቅርቦት በሌለበት ሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ፍሰት የጓሊት መጎተቱ እውነት ነው፡፡ የተፈለገውን ያህልም ሊሆን አይችልም። ከእኛ ሀገር አኳያም በዋነኛነት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ማምጣት የሚፈለገውን ኢንዱስትሪ- መር ኢኮኖሚ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሽግግር ስኬት የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሊኖረው የሚችለውን ጠቀሜታ መገመት አዳጋች አይደለም፡፡

ታዲያ ድህነትን አምርሮ የሚጠላው ህዝባችን ታላቁ የህዳሴ ግድብ ትርጉም ምን ሊሆን እንደሚችል የሚገነዘብ በመሆኑ፣ እዚህ ጉዳይ ላይ ብዙም ማለት የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም መላው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለጀመሩት የፀረ - ድህነት ትግል ምላሽ መስጠት የሚያስችለው መሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ለውጤታማነቱ የሚያካሂደው ርብርብ በቂ ማስረጃ ስለሚሆን ነው፡፡

እርግጥ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ጠቀሜታ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ከግድቡ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይልን ለጎረቤት ሀገሮች በመሸጥ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ የሀገሪቱን ፍላጎት ከማሳካት አኳያም በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በአንድ በኩል የውጭ

ምንዛሬ ማስገኛ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሁሉንም ጎረቤት ሀገሮች የኃይል አቅርቦት የሚያሟላ በመሆኑ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያጠናክር ሀገራዊ ኩራት ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ሀገራችን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጪያ ግድቦች በሰጠቸው ከፍተኛ ትኩረት የሃይል አቅርቦት እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ለጅቡቲና ለሱዳን በመሸጥ የተገኘውን ዘርፈ ብዙ ውጤት መመልከቱ ከበቂ በላይ ማሳያ ይመስለኛል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለጅቡቲና ለሱዳን መስጠት በተቻለው የኤሌትሪክ ሃይል የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም የሀገራችን ማነቆ የሆነውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት በመጠኑም ቢሆን ሊያቃልል የሚችል መሆኑ አይታበይም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ለሚያተኩረው የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችንን በተግባር ከማሳየት ባሻገር፤ ለቀጣናው ኢኮኖሚያዊ ትስስር መጎልበት የሚያበረክተው አስተዋጽኦም በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ለምን ቢሉ ኢትዮጵያም ሆነች ጎረቤቶቿ እኩል ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የቻሉበት ተግባር በመሆኑ ነው፡፡

ይህ ሁኔታም በአንድ በኩል ሱዳንና ጅቡቲ የሃይል አቅርቦት ችግራቸውን በማቃለል ልማታቸውን ለማፋጠን የሚያስችል አቅም መፍጠር ሲችሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገራችንን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ችግር የማቃለል ሚናው ሁሉም ሀገሮች ለሚያደርጉት ዕድገትን የማስመዝገብ ጥረት በቂ ምላሽ በመስጠት በጋራ የማደግ ዕድልን ማጎናጸፍ አስችሏል፡፡

በመሆኑም የኢኮኖሚ ትስስሩ የቀጣናው ልማትን የማረጋገጥ ራዕይን ከማሳካት ባሻገር ሰላምን ከማስፈን አኳያም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ በተግባር መረጋገጥ የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ደግሞ በቀጣናው ሀገራት መልካም ግንኙነትና በአሁኑ ጊዜ እየታየ ያለውን ሰላምና መረጋጋት በእማኝነት ማቅረብ የሚቻል ይሆናል፡፡

ከዚህ አኳያ ሀገራችን በተከታታይ ከገነባቻቸው የኤሌትሪክ ሃይል ማመንጫዎች ከተገኘው አነስተኛ የሃይል አቅርቦት ለጎረቤት ሀገሮች በመስጠት የተገኘው ዘርፈ ብዙ ጥቅም የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ፤ ሌሎች የጎረቤት ሀገሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለሆነ የጋራ ተጠቃሚነቱ ከመጎልበቱ ባሻገር ፈጣን ልማትን የማምጣት፣

አስተማማኝ ሰላምን የማስፈን እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ስር እንዲሰድ የሚያደርግ ብሎም ሀገራዊ ራዕይን ለማሳካት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር አያጠያይቅም፡፡

የህዳሴው ግደብ ፋይዳ ከዚህም በላይ ነው፡፡ በተለይ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በመካሄድ ላይ ለሚገኘው ጥረት ውጤታማነት የሚያበረክተው ድርሻ የላቀ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ግድቡ ለአሳ ምርት ምቹ በመሆኑ በአካባቢው ለሚገኙ አርሶ አደሮችና ለዜጎች የስራ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር፤ ለሀገራዊው የእህል አቅርቦት ማደግ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛና ለምግብ ዋስትናችን መረጋገጥ የሚጫወተው ሚና የላቀ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ግድቡ በኃይል አቅርቦት አማካኝነት ከሚያስገኘው ገቢ በተጨማሪ፤ በቱሪስት መስህብነትም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን ማስገኘት የሚችል ሀገራዊ ሀብት ነው፡፡ መቼም በቱሪስት መስህባቸው አማካኝነት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማግኘት የሀገራቸው ገቢ ማሳደግ የቻሉ የዓለማችን ሀገሮች ቁጥር በርካታ መሆናቸው ሁላችንም የምናውቀው ዕውነታ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም ሩቅ መሄድ ሳያስፈልገን የቅርብ ጎረቤታችን ኬንያ እንኳን ከዘርፉ ምን ያህል ተጠቃሚ በመሆን ላይ እንዳለች የምናውቀው ነው፡፡

በርግጥ ግድቡ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚኖረውን ሀገራዊ ፋይዳ በጥቂቱ ለመጠቃቀስ ሞከርኩ እንጂ፤ በአሁኑ ወቅትም እያበረከተው የሚገኘው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን በማስረጃ አስደግፈን ልናየው እንችላለን፡፡ የግድቡ ግንባታ ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ መሰረተ ልማት ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት ብቻ ከስድስት ሺህ ለሚበልጡ ኢትዮጵያዊያን የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡ በቀጣይም እስከ አስራ አንድ ሺህ የሚደርሱ ዜጎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታን ተከትሎ የሚፈጠረው የዕውቀት ሽግግር ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በግንባታ ሥራው ላይ የተሰማራው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚያካብተው ዕውቀትና ክህሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ እናም በሀገራችን እየተካሄደ ለሚገኘውና ወደፊት ለሚካሄድ የኃይል ግንባታ ሥራ ልምድና ዕውቀት ያለው የሰው ሃይል ከማፍራት አኳያ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛነ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በግንባታ ስራው ላይ በመሳተፍ ላይ የሚገኙት ዜጎች በአለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የሃይል ግንባታ ስራዎች ላይ በመሰማራት ገቢያቸውን ለማሳደግ የሚችሉበት ዕድል ይፈጠራል። ለሀገሪቱም የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሚጫወቱት ሚና በአዎንታዊነቱ ሊገለጽ የሚችል ይሆናል፡፡

እንግዲህ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ የመሆኑን ጉዳይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያውቀው ከመሆኑ ባሻገር ለግንባታው ስኬታማነት የየድርሻውን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ የግድቡ ግንባታ መጠናቀቅንም በጉጉት የሚጠባበቅ ስለመሆኑ ቅንጣት ያህል የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

እዚህ ላይ ግን መነሳት ያለበት አንድ ቁም ነገር ያለ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም በውኃው የመጠቀም መብታችንን ለዘመናት ሲያደናቅፉ የቆዩት ግብጾች ለአላማቸው ስኬት የዜጎቻቸውና የመገናኛ ብዙሃናቸው ድርሻ ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበር ነው። የእኛ ዜጎችና መገናኛ ብዙሃንስ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ከማሳወቅና ከማስገንዘብ አኳያ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?...እስቲ የእኛዎቹን በማስቀደም የጉዳዩን አሳሳቢነት እንመልከት፡፡

መቼም ነገር ነገር ያነሳዋል አይደል የሚባለው?...እናም በቅርቡ ከወጡት መረጃዎች ብንነሳ እንኳን በሀገራችን የሚገኙ የመንግስትም ሆነ የግሉ የመገናኛ ብዙሃን በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ዙሪያ የሚያከናውኑት ዘገባ እናሳ መሆን ሲገለጽ ይስተዋላል፡፡ እንደሚታወቀው የመገናኛ ብዙሃን ህዝብን በማሳወቅና በማስተማር ለሀገራዊ ልማቱ መፋጠን የበኩላቸውን ድርሻ የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ አንጻር ጅምሩ የለም ባይባልም ተሳትፏቸው ግን አነስተኛ ነው፡፡ በተለይም ለሀገራችን ዕድገት ወሳኝ እንደሆነ የሚታመነው የልማት ጋዜጠኝነትን ከመተግበር አኳያ በጣት ከሚቆጠሩ መገናኛ ብዙሃን በስተቀር አብዛኛዎቹ የግል ሚዲያዎች የራሳቸውን አጀንዳቸውን ለማስፈጸም የሚሯሯጡ ሆነው ይታያሉ፡፡

እንደሚታወቀው የልማት ጋዜጠኝነት በሀገሪቱ የሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን በመከታተል መረጃን ለህዝቡ የማድረስ ፤በመሰረተ ልማት ግንባታዎች የሚታዩ በጎና ደካማ ጎኖችን በመገምገም ጠንካራ ጎኖቹ የበለጠ የሚጎለብትበት ደካማ ጎኑ ደግሞ የሚቀረፍበትን ሁኔታ በመዘገብ ለመንግስት አካላትና ለምልዓተ ህዝቡ በማድረስ ለሀገራዊው ልማት መፋጠን ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር ነው፡፡ ይህም ታክስ ከፋዩ ህዝብ

የሚያወጣው ገንዘብ በትክክለኛ ቦታ ላይ ወዋሉን የሚገነዘብበት፣ ሀገሪቱን የሚመራው መንግስትም የመደበው ሰብዓዊና የገንዘብ ሀብት በተገቢው መንገድ እየተካሄደ እንደሚገኝ የሚገነዘብበትና እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚችልበትን ሁኔታ በመፍጠር ተፈላጊውን ዕድገት ማስመዝገብ የሚቻልበትን ዕድል ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ለሀገራችን ዕድገት እንዲሁም ህዝባችን ከገባበት የድህነት አረንቋ የሚወጣበትን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥረው የልማት ጋዜጠኝነት፤ በተለይ የኤስያ ሀገሮች ውስጥ ተሞክሮ ውጤታማ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ታዲያ የራሳችን አጀንዳ ለማሳካት የሚሯሯጡት፣ ከፍ ሲልም ልማቱን አኮስምነው የሚያዮት የሀገራችን የግል ህትመት ሚዲያዎች ወዴት እያመሩ እንደሆነ ቆም ብለው ሊገነዘቡት ይገባል ባይ ነኝ፡፡

በእርግጥ ሀገራችን ለሠላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባህል ግንባታ ትኩረት ሰጥታ ለስኬቱም በመንቀሳቀስ ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን አስተዋጽኦ የላቀ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ታዲያ በእኔ እምነት አብዛኛዎቹ የሀገራችን የግል መገናኛ ብዙሃን ከዚህ እውነታ እጅጉን ርቀው መገኘታቸው አስገራሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሀገራዊው የሰላምና የልማትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እዚህ ግባ የሚባል የሚባል ባለመሆኑ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የመላው ኢትዮጵያውያን ሀብት የሆነውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የአንድ ፓርቲ እንደሆነ አስመስለው ግንባታውን ለማጠልሸት የሚጥሩ የህትመት ውጤቶች መኖራቸው ከተለያዩ ዕትሞቻቸው መረዳት ይቻላል– ምንም እንኳን ሚዛናዊው፣ ጊዜውን ለአሉባልታ ሳይሆን ለወሬ ብቻ የሚያውለውና የግድቡን ፋይዳ የሚገነዘበው የሀገራችን ህዝብ ጆሮውን ሊያውሳቸው ባይፈቅድም፡፡

እዚህ ላይ ግን አንድ ጥያቄን ማንሳት ያስፈልጋል– 'በርግጥ የግብጽ መገናኛ ብዙሃን የአባይን ጉዳይን የሚያዩት እንደኛዎቹ ይሆን?' የሚል። ታዲያ ምላሹ 'በፍጹም' የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በኋላ ስለወንዙ ጥቅም ከማስተማርና ከማሳወቅም በላይ ሰብከዋል ማለት ስለሚቻል ነው፡፡ አባይ ለግብጽ ከፈጣሪ የተሰጠ ገጸ በረከት የመሆኑን አመለካከት ህዝባቸው አእምሮ ለመቅረጽ ከመሞከር አልቦዘኑም፡፡ በዚህም ባይሳካላቸውም የሀገራቸው ህዝብ በአባይ ወንዝ ሊኖረው የሚገባ አመለካከት ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ እንዲሆን ጥረዋል። ምክንያቱም ጥቂት

የማይባለው የግብፅ ህዝብ እስከዛሬ ድረስ ያሉት ገዥ መደቦቹ የአባይ ጉዳይን እንደ የስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ "ዕፅ" እየተተቀሙበት መሆኑን እየተገነዘበ በመምጣቱ ነው።

ለነገሩ የመገናኛ ብዙሃኖቻቸውን አነሳን እንጂ በደራሲዎቻቸው አማካኝነት በአባይ ዙሪያ የተጻፉ መጽሐፍት ቁጥርም እጅግ በርካታ መሆኑ ነው የሚገለጸው፡፡ የሀገሪቱ ምሁራን ቀዳሚው ምርጫ በአባይ ዙሪያ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ ለህዝቡ ማድረስ መሆኑን ስንመለከት ለሀገራቸው ምን ያህል ተቆርቋሪ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ የሀገር ፍቅር እንዲህ ነው፡፡ እናም ባለፉት ዘመናት በሚሄዱበት ቦታዎች ሁሉንም ለማሳመን ያደረጉት ጥረት በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

አዎ! ትናንት የግብፅ መገናኛ ብዙሃንና ምሁራን የቅኝ ግዛት ውሎችን እየጠቀሱ በአባይ ውኃ የመጠቀም መብታችንን አሳጥተውን ቆይተዋል፡፡ ውኃውን ለብቻቸው ያለ ከልካይ መጠቀም ችለዋል፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሲያካሂዱት የቆዩት የማደናቀፍ ስራም ዘመናትን ቢሻገርም እስከ ወዲያኛው ግን ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ ምክንያቱም በውኃው የመጠቀም መብታችንን ለማረጋገጥ በኢፌዴሪ መንግስት የተካሄደው ሁለንተናዊ ጥረት ለውጤት መብቃት በመቻሉ ነው። የዘመናት ቁጭት የሆነው አባይ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ምላሽ ለማግኘትም በቅቷል፡፡

ይሁን እንጂ የህዳሴው ግድብ በመላው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ንቁ ተሳትፎ መገንባት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ግብጾች ግንባታውን ለማደናቀፍ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ሀገሪቱ ምንም እንኳን በቀውስ ላይ የምትገኝና የፖለቲካ ልዩነት ያንዣበበባት ብትሆንም፤ የአባይ ጉዳይ ግን አንዳች ልዩነት ሲስተዋልበት አይታይም፡፡ ዛሬ ስልጣን ላይ ያለው የአድሊ መንሱር መንግስት ልክ እንደ ቀደምት የሀገሪቱ መሪዎች "የዓባይ ውሃ ቅንጣት ያህል ሊነካብኝ አይገባም" የሚል ተመሳሳይ ዜማን እያቀነቀነ ነው–ሀገራችን የማታውቀውን የቅኝ ገዥዎችን ውል እየጠቀሰ። እርግጥ ይህ ሁኔታ በውስጣዊ ችግራቸው ላይ ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው ፓርቲዎችም ሆኑ የየራሳቸውን አጀንዳ ያነገቡ የመገናኛ ብዙሃን አባይን በተመለከተ አንድ ቋንቋ መናገር መቻላቸው፤ በገዛ ሀገራቸው ልማት ላይ በአሳፋሪነት ተፃርረው ለቆሙ አቻ ፓርቲዎችም ሆነ ልክ እንደ ግብፅ የመገናኛ ብዙሃን ግድቡን በደፈናው ለሚቃወሙ የግል ሚዲያዎች ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ሀገራዊ ጥቅማችን የሚከበረው ሁሉም ዜጋ ያለውን ሲያበረክት በመሆኑ፤ የዓባይን ጉዳይ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ

የሀገራችን አምባሳደር ሆነን ለዓለም ማሳወቅ የዜግነት ግዴታችን መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም። ነገርዬው አበው “ጋን በጠጠር ይደገፋል” እንዲሉት ዓይነት ነውና። አበቃሁ።